የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)

Amara Survival for Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)



| ቅጽ ፳ | ቁጥር ፪ | ኅዳር ፲፪ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም | በየአሥራምስቱ ቀን ዘወትር ኅሙስ ኅሙስ የሚወጣ |
|---|---|---|---|



ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደግ!

# ጠቅደላ

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

## የዐኅኢአድ ልሣን

## የዐማራው ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

**ሁለት ሺ አሥር የትግሬ-ወያኔ ከፋፋይ አገዛዝ ማክተሚያው ወይስ እንዳለፉት ሁሉ ሞቶ መነሻው?**

ከመነሻው ወያኔ አንግቦት የተነሳበት ዓላማው የተሳሳተ፣ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህም የተሳሳተ ዓላማ በተለያዩ ወቅቶች ፣ዓላማውን ያልደገፉ ቡድኖች ባነሷቸው ጥያቄዎች የመከፋፈል እና የመፈራረስ አደጋዎች በከፍተኛ ደረጃ እየጋረጡበት እንደ እባብ ሞቶ አፈር እየላሰ ከዚህ የደረሰ መሆኑ ይታወቃል። የትግሬ-ወያኔን ለመበታተንና ለማፍረስ የሚችሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ተሟልተው እያለ፣ ገፍቶ የሚጥል ጠናካራ አገራዊ ዕራይ ያነገበ ድርጅት አለመኖር፣ላለፉት 43 ዓመታት አገርና ትውልድ የሚያጠፋ ሥራ እንዲሠራ ሠፊ ዕድል አገኘ። በራሱ ውስጥ የተፈጠሩትን ችግሮች በመጠቀም ገፍቶ መጣል ባለመሞከሩ፣ ወያኔ ድክመቶቹን የጥንካሬውና የመታደሻው መገለጫዎች እያደረገ ሕዝብን ለማተለል ተጠቀመበት። የ1969 እና 1970 ዎቹ «የሕንፍሽ ሕንፍሽ» የትግራይ አውራጃዎች ልዩነት እንቅስቃሴ፣ የድርጅቱን መሥራቾችና መሪዎች የነበሩት አረጋዊ በርሄና ግደይ ደብረጽዮን ከድርጅቱ የማባረር ሂደት፣ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማግሥት በነተወልደና መለስ የተፈጠረው ክፍፍል የትግሬ-ወያኔ ወደ መቃብር አፋፍ ያደረሱት ክስተቶች ነበሩ። ለነዚህ ችግሮች ያበቁትም ጠንካራ ተቃዋሚ ኖሮና በርሱ ተገፍቶ ሳይሆን፣ ዓላማቸው ስሕተት በመሆኑ፣ኢትዮጵያዊነት በመንፈስ፣ ዐማራው በፀሎት፣ በትዕግሥትና ትዕግሥቱን እንደፍራት ሲቆጥሩት ደግሞ ከ2008 ዓም ጀምሮ በመጡበትና ሊገባቸው በሚችለው ቋንቋ ማነጋገር መጀመር ለሌላ ዙር የትግሬ-ወያኔ ክፍፍልና መፈራረስ ሠፊ በር እንደከፈተ እያየን ነው።

በሌላ በኩል ካለፉት 3 ዓመታት ጀምሮ በመካከለኛው የአገሪቱ ክፍለ-ሀገሮች፣ አውራጃዎችና ወረዳዎች የተቀጣጠለው የኦሮሞ ወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተከታታይነት፣ ከዐማራው የኅበዝ አለቆች እንቅስቃሴ ጋር ጎን ለጎን መፋፋም፤ «ከየትኛውም ጊዜ ከነበሩት አገዛዞች በበለጠ የሕዝቡን አንድነት አረጋግጫለሁ፣ ሰላም አስፍኛለሁ፣ ከፍተኛ የሆነና በያመቱ 11% ዕድገት አስመዝግቤአለሁ፤ዲሞክራሲያዊ አሠራርና ባሕል እየገነባሁ ነው፣ የዚህም መሠረቱ ሕዝቡ ወዶ ያጸደቀው ሕገ-መንግሥት የአገዛዙ መመሪያ በመሆኑ ነው» እያለ፣ በሚለፍፍበት ጊዜ፣ ሕዝባዊ እንቢተኝነቱ በመላ አገሪቱ ዳር እስከ ዳር መቀጣጠል ያሳደረበት ከፍተኛ ጫና ፣የሰላምና የብልጽግናዬ መስተዋት ነው የሚለውን «ሕገ-መንግሥት» አግዶ ወታደራዊ አገዛዝ ለ10 ወሮች አስፍኖ ሕዝቡን በገፍና በግፍ መግደሉ፣ ማሰሩና ማሰቃየቱ ይታወቃል።

ይህ ሕዝባዊ አመጽ በ2009ዓም ላይ በመላ አገሪቱ መስፋፋትና ፣ከሁሉም በላይ ፣«ዐማራው ላይነሳ አከርካሪውን መተነዋል»፤ «ዐማራና ኦሮሞን እሳትና ጭድ አድርገናቸዋል»፣በማለት ኢትዮጵያን እስከ ወዲያኛው በእኛ ፍልጎት ያሻንን እናደርጋታለን፣ ካልሆነም አፈራርሰናት ወደ ትግራይ-ትግሪኝ ግዛታችን እንገባለን ብለው በሚፏልሉበት ወቅት፣ እሳትና ጭድ እንዲሆኑና በአጥፊና ጠፊነት ጎራ እንዲሰለፉ

# መቅደላ

ያደረጓቸው ዐማራና ኦሮሞ ነገዶች ሰምና ፈትል፣ውኃና ወተት በመሆን፣ ተነጥለው እንደቆዩ ላምና ጥጃ እምቧ እያሉ በናፍቆት መተቃቀፍ የወያኔን በሁለቱ ነገዶች ፍቺ ዕድሜ የማራዘም ሕልም ወደ ቀን ቅዠት እንደለወጠው እያስተዋልን ነው። ገድለን ቀብረነዋል ያሉት ዐማራ መቃብር ፈንቅሎ ፣ትፋሽ ስቦ፣ በከፍተኛ እልክ ማንነቱንና እርሱነቱ ለማሳየት በመጡበት መንገድ በመጓዝ፣ በሚገባቸው ቋንቋ ማነጋገር ሲጀምር፣ከሁሉም በላይ ኢሉባቡር ላይ የወያኔ ሰላዮች በደንጋይ ተወግረው መገደል ወያኔንና ተከታዩን ብርክ ከቶታል። ይህም የወያኔን አመራር ከሁለትና ከዚያም በላይ ሰንጥቆታል። «እናቴ ትግሬ ባልሆንሽ የሚባልበት ዘመን ይመጣል» የሚባለው በትግራይ ሕዝብ ዘንድ በፍርሓት የሚነገረው የቆየ ትንቢት መፈጸሚያው ወቅት ላይ ተደርሷል የሚሉት አባባሎች በስፋት በማኅበረሰቡ ውስጥ መነገር፣ የወያኔን ባለሥልጣን ነን ባዮች ብርክ ከቷል።

በዐማራውና በኦሮሞው ወጣቶች ከእልክና ከቁጭት የመነጨው የፀረ-ወያኔው እንቅስቃሴ፤ ከዓመት ዓመት ሥፋትና ጥንካሬ እያገኘ መጓዝ ያሰጋው የወያኔ ጥርቅም ፣ እንዳለፉት ሁሉ ይህን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመግታት የተለያዩ እርምጃዎች የሞት ሙቱን ለመውሰድ በጥድፊያ ላይ ይገኛል። የሚወስዳቸው የአፈና እና የዕመቃ ዘግናኝ እርምጃዎች፣ እንዳለፉት ሁሉ የትግሬን የበላይነት ለማስጠበቅ እስከተቻለ ድረስ ማናቸውንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰድ የማይመለስ መሆኑ ካለፉት ድርጊቶቹ መገንዘብ ከመቻሉም በላይ፣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴው ያሳደረበት የፍርሃት ቆፈን ማየል እርምጃው ካለፉት የከፋ ጅምላ ጭፍጨፋ እንደሚሆን የተለያዩት መረጃዎች ያሳያሉ።

ለሚወስዳቸው ርምጃዎች ጅምላና ፍፁም አረመኔ መሆን ማሳያው፣ የወያኔ «እህት እና አጋር ድርጅቶች» የሚባሉትን ኦሕዴድና ብአዴን እንደ ድሮው የተለመደ የባንዳነት ተግባራቸውን ወያኔ በሚሻው መልኩ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ባሳደረበት የተከዳን ስሜት የቂምና «እኛ ከሌለን ሁሉም ነገር ይጥፋ» በሚል ተስፋ መቁረጥ ስሜት የሚወሰድ መሆኑ ነው። የወያኔ የአማርኛና የኦሮምኛ ቋንቋ ክንፍ የወገን መፍለጫና መቁረጫ እጀታ የሆኑት ድርጅቶች ከ1997 ምርጫ ውጤት ተከትሎ በገፍ ድርጅቶቹን እንዲቀላቀሉ የተደረጉት የዐማራና የኦሮሞ ወጣቶች፣ ነባሮቹን የወያኔ ጌኛዎች በአስተሳሰብም፣ በቁጥርም የቀደሟቸው በመሆኑ፣ እንዳለፈው ወያኔ አድርግ ያላቸውን ለማድረግ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ፣ «እኛም የሥልጣን ተጋሪ፣ የልማት ተቋዳሽ ልንሆን ይገባናል፤ ወያኔ አምባገነን ከመሆን አልፎ፣ በሙስና የተዘፈቀ ድርጅት ሆኗል፣ ስለሆነም መታደስና በሕዝብ ፍላጎት ተገዥ ሊሆን ይገባል» የሚሉ ድምፆችን ማስተጋባት መጀመራቸው በወያኔና በእህት ድርጅቶቹ መካከል መፈራረቅ ፈጥሯል።

የወያኔ እህትና አጋር ድርጅቶች የሚባሉት፣ ከታዛዥነት ለመውጣት የሚያሳዩት የጉቢነት መንፈስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መምጣት፣ ወያኔንና አጋር ድርጅቶች የሚባሉትን ግራና ቀኝ እያቆመ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ወያኔ ከመለስ ሞት በኋላ ነፍስ ያለውና በሁሉም ትግሬ ዘንድ ተቀባይነትና ታማኒነት ያለው መሪ ማውጣት አለመቻል፣ በአገዛዙ ውስጥ የሰፈነው ሙስና ጋር ታግዞ፣ የትግሬ-ወያኔ እንዳለፉት ሁሉ አፈር ቅሞ ሊነሳበት ከማይችልበት ደረጃ ላይ አድርሶታል። የዚህም ምክንያቱ አገሪቱንና ሕወሓትን ለገጠሟት ችግሮች የሚሰጡዋቸው የመፍትሔ አቅጣጫዎች የድርጅቱን አባላት ከሁለትና ከዚያም በላይ መከፋፈሉ ነው። ይህ ክፍፍል ከድርጅቱ አልፎ በሕዝቡ መሀል ገብቷል። የዚህ ማሳያ የሚሆኑት፣ የቀድሞው የወያኔ የአየር ኃይል አዛዥ የነበረው «የጄኔራል» አበበ ኃይለሥላሴ፣ የቀድሞው ኤታማጆር ሹም የነበረው «የጄኔራል» ጻድቃን ገብረተንሣይ፣ የንጋት ጮራ በሚል መጠሪያ የወጡ ጽሑፎች፣ የአረና ትግራይ የተቃውሞ ሰልፍ፣ በውጭ በሚኖሩ ትግሬዎች ስም የተዘጋጁና ለሕዝብ የቀረቡ ጥሪዎች የክፍፍሉን ዓይነት እና በትግራይ ሕዝብ ውስጥ የሰፈነውን ፍርሓቻ የቱን ያህል እንደሆነ ያሳያሉ።

የ2010ሩ በወያኔ ላይ የተጋረጠው ሞት ጠሪ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ ባለፉት ከገጠሙት የሚለየው፣ተቃውሞው ከውስጥና ከውጭ መሆኑና ሕዝባዊ እንቢተኝነቱ አመጽን የቀላቀለ መሆኑ፣ ሞትን የማይፈሩ ወጣቶች ከአፈሙዝ ፊት ለፊት በሞቆም አይቀሬውን ሞት በክብር ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸው ነው። ይህም በመሆኑ የአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ በሁለት ዘመን ጠገብ በሆነ አደረጃጀት ነገዳቸውን ተከታይ ባደረጉ የትግሬና የኦሮሞ ብሔርተኞች መካከል የከረረ የሥልጣን ፍትጊያ ባንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ዐማራው ኀልውናው አደጋ ላይ ነው የሚሉ ወገኖች በውስጥና በውጭ የወያኔ አገዛዝ የእግር እሳት መሆን፣ የዐረቡ ዓለም በጦርነት መታመስ ያሳደረው ጫና፣ ወያኔ ሆን ብሎ በሶማሌና ኦሮሞ ነገዶች መካከል ያቀጣጠለው የዘር ፍጅት አቅጣጫውን ወደ ወያኔ ማዞር፣ የወያኔ የነፍስ አባት የሆኑት ምዕራባውያን ለጋሽና አበዳሪ መንግሥታት በአገዛዙ ላይ ጥያቄ ማንሳት እና አማራጭ ኃይል ማማተር መጀመራቸው፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ መሽመድመድና የብር ዋጋ ማጣት፣ የሥራ አጡ ሠራዊት ቁጥር ጣራ ማለፍ የዘረኛው አገዛዝ መድኃኒት የሌለው የሆድ ቁርጠት፣ የእራስ ፍልጠት ሆኖበታል።

ወያኔ ከዚህ የሞት ሽረት ግብግብ ውስጥ በአሸናፊነት ለመውጣት የተለያዩ ሥልቶችን በመቀየስ የሙት ሙቱን በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። የመጀመሪያ ስልቱ አነሳሁት ያለውን ወታደራዊ አገዛዝ መልሶ ቢያውጅ የሚያስከትልበትን ዲፕሎማሲያዊ ጫና በመፍራት፣« የብሔራዊ ደኅንነት» ኮሚቴ ለሚለው መዋቅሩና በቁጥርም ሆነ በኃላፊነት ወሣኝ በሆኑት ቦታዎች በወያኔ ነባር አባሎች የተሞላውን ከብሔራዊ እስከ ቀበሌ ባዋቀረው ቡድን ሕዝቡን የፈለገውን እንዲያደርጉ የሚያስችል ያልታወጀ ሥልጣን ሰጥቶ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን እንዲያስቆሙ አዟል። የዚህ አፋኝና ገዳይ ቡድን ዝርዝር የአፈጻጸምም መመሪያ በመቸውም ጊዜ ሆኖ በማያውቅ መልኩ ሾልኮ ከሕዝብ እጅ ገብቷል። ይህ በራሱ የወያኔ አገዛዝ ከውስጥ የተቦረቦረና የላሸቀ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ይኸም ሆኖ፣ ባለው ያፈና መዋቅሩ አጥፍቶ የመጥፋት ተግባሩን መቀጠሉ የማይቀር ነው።

ሁለተኛው ሥልት እራሳቸው በፕሮግራም ቀርጸው፣ በኃይል በታገዘ ፕሮፓጋንዳ «እሳትና ጭድ» እንዲሆኑ፣ ያማራና የኦሮሞ መጭው ትውልድ ጎን ለጎን እንዳይቆም የሚያስችል የጥላቻና የቂም ሀውልት «አኖሌ» በሚል ስም መገንባታቸው ግልጽ ነው። ኦሮሞው ዐማራውን

# ጠቅደላ

እንዲያጠፋ ብዙ ርቀት የተጓዘ የጥፋት ሥራ የሠሩ መሆኑ ይታወቃል። እንዲሁም «የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት ዐማራ ነው፤ ዐማራ ካልጠፋ የትግራይ ሕዝብ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም» በማለት ላለፉት 44 ዓመታት ዐማራውን እንደ አውሬ በማደን ሁለቱን ነገዶች ትግሬ አጥፊ፣ ዐማራን ጠፊ አድርገው ጎራ ለይተው እንዲቆሙ ማድረጋቸው ማንም አይስተውም። በዚህ ጥረታቸውም ከ5 ሚሊዮን ዐማራ በላይ እንዲጠፋ አድርገዋል። ይህን ሁሉ ግፍ በትውልድና በአገር ላይ ከሠሩ በኋላ፤ ዛሬ ማጣፊያው ሲያጥራቸውና የፈለጉትን ሁሉ አድርገው፣ በፈለጉት ሰዓት ወደ ትግራይ ትግሪኝ መንደራቸው ተገንጥለው ለመሄድ ያቀዱትን የቆየ ዓላማ በነርሱ ሰዓት ሳያከናውኑ ሕዝባዊ እንቅስቃሴው ስለቀደማቸው፣ ይህን ለማርገብና ሁሉም ነገር በነርሱ ፈቃድ እንዲሆን ለማድረግ «የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ አንድነት፣ኢትዮጵያዊነት» የሚሉ መፈክሮችን አንግበው ተነስተዋል።

ለዚህም ተፈጻሚነት ባንድ በኩል የብሔራዊ ደኅንነቱን መዋቅር በማጠናከር አፈናና ግድያውን እያካሄደ፣ በሌላ በኩል በኦሕዴዱ ሊቀመንበርና «የኦሮሚያ» ክልል ተብየው ፕሬዚዳንት የሚመራ ቡድን  ወደ ባሕርዳር ልኮ ላለፉት 26 ዓመታት ሲወገዝ የነበረው አንድነትና ኢትዮጵያዊነት እንደ አዲስ ተጠማቂ ክርስቲያን ፣አንድነት!፣ አንድነት!፣ኢትዮጵያዊነት!፣ ኢትዮጵያዊነት!፣ ማለትን የንግግራቸው መክፈቻና መግቢያ እንዳደረጉት እያየንና እየሰማን ነው። ዐማራውና ኦሮሞው ውኃና ወተት ሆነው አንዱ በሌላው ውስጥ መኖር ከጀመሩ ቢያንስ 600 ዓመታት ያህል ያስቆጠሩትን የኢትዮጵያ ምሰሶ፣ ማገርና ጭምጭ ሆነው የተዋቀሩን፣ ላለፉት 27 የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ሆን ተብሎ በተናፈሰ ፕሮፓጋንዳና ፖለቲከኞቹ ሁለቱ ነገዶች የጠላትነት ስሜት ውስጥ ገብተው አጥፊና ጠፊ እንዲሆኑ ያያዙት እሳት፣ ቆስቋሾቹን ማቃጠል ሲጀምር፣ ወያኔና አጋሮቹ የአንድነትና የኢትዮጵያዊነት ነጠላ ዜማ ማዜም ጀምረዋል።

ወያኔን ወደዚህ ዓይነቱ  የነፍስ አድን  የትግል አቅጣጫ እንዲያዞር ያስገደደው የሚከተሉት እንደሆኑ ይታመናል። አንደኛ ኦሕዴድ እንደ ቀድሞው የወያኔ ታማኝ ወዶ ገባ አሽከር ከመሆን ወጥቶ፣« እኛም ሥልጣን ያስፈልገናል? የወያኔ አምባገነንነትና የበላይነት ይብቃ?» የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳት እና የሁሉም የኦሮሞ ድርጅቶች ኦሕዴድን ጨምሮ በአንድነት በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ መቆም የወያኔ እጇታ የሆነውን «ኢሕአዴግ» የተሰኘውን ስብስብ ውሣኔ ተፈጻሚነት ሽባ ማድረጉ ነው ። ሁለተኛው «ዐማራው የትግሬ ጠላት ነው» ብለው ፈርመው «ኢሕዲን» በሚል ስም ተሰባስበው የወያኔ መሣሪያ የነበረው የነአዲሱ ለገሠ፣ ተፈራ ዋልዋ፣የነስምዖን በረከት፣ የነሕላዊ ዮሴፍ፣ የነታደሰ ጥንቅሹ፣ የነካሣ ተክለብርሃን ቡድን፣ ከ1986 ጀምሮ ባንድቀን ጀንበር ወደ «ብአዴን» የተቀየረው፣ ከነባሮቹ የባንዶቹ አመለካከት በመላቀቅ «ዐማራ ባልሆኑ ሰዎች ብአዴን ሊመራ አይገባውም? ብአዴን በዐማራው ልብ ውስጥ እንዲኖር ከተፈለገ የነስምዖን በረከት መሰል ግለሰቦች ከብአዴን ይውጡ? ወያኔ በዐማራው ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ዘንርን መነሻ ያደረ ጥቃት ይቁም፤ ማለት መጀመራቸውና ከሁሉም በላይ የወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ገዝፎ መውጣትና የኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ አብሪ ጥይት ጎንደር ላይ መተኮስ፣ ብአዴን ለወያኔ የነበረውን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ከቶታል። ባጭሩ የብአዴን አመራር ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ያለው ወያኔ በዐማራው ላይ የሚያደርሰው በደል ይቁም የሚል ድምፅ ማሰማትና የወያኔን የሁሉም ነገር ወሣኝነት መቃወም፣ ለወያኔና ለትግራይ ሕዝብ መገለልን በማስከተሉ፣ ሕዝቡንና ድርጅቱን ለፍርሃት አጋልጧል። ከሁሉም በላይ በ2008 ጎንደር ላይ፣ በወያኔ ሰላዮች ላይ ሕዝቡ የወሰደው  ርምጃ፣ በ2010 ኢሉባቡር ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ በወያኔ የስለላና የአፈና መዋቅር ሠራተኞችን የራሱን ማኅበራዊ ፍርድ ሰጥቶ ፣በደጋይ ወግሮ መግደሉ መሰማት የወያንኔ ቡድን ከፍተኛ የሆነ ፍርሃትና የመገለል ስሜት ውስጥ ከቶታል።

ይህም ወያኔ ትግሉ ከውስጥ ከኦሕዴድ (የኦሮሞ ድርጅቶች)፣ ከብአዴን የነቁ ክፍሎች ጋር የሥልጣን ግብግብ እንዲገባ አድርጎታል። ይህን ግብግብ ለማርገብና ሥልጣኑን መልሶ ለማደላደል ጊዜ መግዣ የሆነ «ተጨፈኑ ላሞኛችሁ» ዓይነት ሥራ እየሠራ ይገኛል። ለዚህም የኦሮማና የዐማራ ሕዝብ አንድነው፣ ዐማራና የትግሬ ሕዝብ አንድነው፣ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ መዝሙሮችን ማዜም ወያኔ ከገባበት ቅራቅር ውስጥ ሁነኛ መውጫው መንገድ አድርጎ ይዞታል። በዚህም መሠረት በወያኔ የስለላ መዋቅር ውስጥ ላለፉት 25 ዓመታት በተለያዩ ደረጃዎች ይሠራ የነበረውንና ያለሕግ ለተገደሉ፣ ለታፈኑ፣ ለታሰሩና ለተሰቃዩ ኦሮሞዎችና ዐማሮች፣ ጋምቤላዎች፣ ሶማሌዎች ወዘተ ተጠያቂ ከሚሆኑት አንዱ የሆነውን ለማ መገርሳን፣ የኦሕዴድ መሪና የኦኮሚያ ክልል ተብየው ፕሬዚዳንት፣ በርካታ የኦሕዴድ አባላትን አስከትሎ ምንጊዜም ቢሆን በዐማራና በኦሮሞ ሕዝብ መካከል እንደ ሕዝብ ጠብ ኖሮአቸው የማያውቁትን እናስታርቅ፣ ሰላም እንፍጠር በሚል ስም ወደ ባሕርዳር መሄዱና ስለኢትዮጵያዊነትና አንድነት እስከዛሬ ከወያኔ ሠፈር ተብለው የማያውቁ ጽንሰ ሀሳቦችን አሰምቶናል። አቶ ለማ መገርሳ ያለው  ሁሉ እውነት በተግባር የሚገለጽ ካልሆነ በንግግሩ የሚከፋ ይኖራል ለማለት ያስቸግራል። የተናገረው የኢትዮጵያ ሕዝብ  ሲል የነበረውና እያለውም ያለ በመሆኑ በንግግሩ ችግር የለም። ችግር የሚሆነው፣ ችግሩን ማንፈጠረው? እንዴትስ ተፈጠረ? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስተን ስንጠይቅ የለማ ንግግር ሁነኛና ትክክለኛ መልስ ይዞ አለመቅረቡ ነው።

ማንም እንደሚያውቀው፣ ችግሩን የፈጠሩት ብሔርተኞቹ ድርጅቶች ሻዕቢያ፣ አነግና ወያኔ በተደጋጋሚ የተሰኔው ማንፌስቶ በሚባል የሚታወቀውን የ1984ቱ የሽግግር መንግሥት ተብየው ቻርተር ሆኖ  እንዲሠራበት መደረጉ ነው። ቀጥሎም ሦስቱ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ የሆኑት ተገንጣይና ብሔርተኛ ድርጅቶች የስምምነት ውጤት የሆነውን  ማኒፌስቶ ወይም ቻርተር፣ከ1987 ዓም ጀምሮ የመንግሥትና የሕዝብ መስተዳደሪያ  እንዲሆን በሕገ-መንግሥት ስም የአገሪቱ ገዥ ሕግ እንዲሆን ተደረገው ነው። ሕገመንግሥቱም  ሆን ተብሎ ኢትዮጵያን ለመበታተን፤ ለመሬት ቅርምት፣ ለዐማራ ዘር ማጥፊያ በሚያመች መልኩ፣ በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ፌደራላዊ አስተዳደር እንዲመሠረት በመደረጉ ዛሬ አገሪቱ ለገባችበት የመበታተን አደጋ ያጋላጣት እንደሆነ ግልጽ ነው። ባጭሩ ወያኔ ሥልጣን በኃይል ከጨበጠ ጊዜ ጀምሮ በሕዝባችን መካከል የሚነሱ ችግሮች መሠረታቸው በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተው ሕገ-መንግሥት፣ የሕገመንግሥቱ ማስፈጸሚያ መሣሪያ የሆነው የአገዛዙ ርዕዮት ዘረኝነት መሆን ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህ ችግሮች፣ ችግር ናቸው ብሎ ያላመነና ለችግሮቹም መፍቻ የሚሆን ስልት ያላዘጋጀ ችግሪቹን ከማባባስ ውጭ ያጠባቸዋል ተብሎ አይታሰብም።

# መቅደላ

የአቶ ለማ መገርሳ ንግግር ኢትዮጵያዊነትን «ሲሻ በሚተው፣ ሲሻ ደግሞ በሚዘወተር የሀሺ ሱስ» መመሰላቸው የሀሳበቸው መነሻ ስሕተት በመሆኑ መድርሻውም ስሕተት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያዊነት ማንነት ነው፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የትውልድ፣ የሰላማና የጦርነት፣ የንግድና የፍልሰት፣ የጋብቻና የጊዲፍቻ፣ የሞጋሳና የአብሮነት ስሜት ውሕድ ሥነልቦናዊ ጥልፍልፍ ቁርኝት ነው። ይህን ቁርኝት ማንም ሊፈታውና ሊለያየው አይችልም። በመሆኑም ኢትዮጵያዊነት ሲሹት የሚይዙት፣ ሳይሹት የሚጥሉት ማንነት አይደለም። ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ማንነት ውስጥ ያለ ፣ቅር ቢሉት የማይቀር፣ ልጣልህ ቢሉት የማይጣል የቀትር ጥላ ነው። ስለሆነም አቶ ለማ ስለኢትዮጵያዊነት የተነሱበት መነሻ ሀሳብ የተዛባ ትርጉም ያለውና ኢትዮጵያዊነት በሰዎች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አድርገውታል። በሌላ በኩል በኢትዮጵያዊነት ላይ የተጋረጠው ችግር መነሻው በልዩነት ላይ የተመሠረተው ሕገመንግሥትና ፌደራዊ አስተዳደር መሆኑ እየታወቀ፣ ስለዚህ ጉዳይ አቶ ለማ ያሉት አንዳችም ነገር የለም። በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች መካከል ከጥንት ጀምሮ የነበረውን አንድነትና አብሮነት ወደ ብጥብጥ እያመራው ያለው አገዛዙ የሚከተለው አድላዊና በሙስና የተዘፈቀ የዘር ፖለቲካ መሆኑ የኦሮሞም የዐማራም ሕዝብ በግልጽ በየአደባባዩ እየተናገረ ነው። ያን ደፍረው በባሕርዳሩ ንግግራቸው ለመናገር አልፈለጉም። ይህ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በኦሮሞና በዐማራ ሕዝብ ፈቃድ የተዘጋጀ ሳይሆን፣ ወያኔ ለገጠመው የከረረ ሕዝባዊ ተቃውሞ ጊዜ መግዣ ለማግኘት በወያኔ ቀደም ብሎ የታሰበበት እንደሆነ የወግ ዕቃው ኃይለማርያም ደሣለኝ ነግሮናል። እና የለማ መገርሳ የባሕርዳ ጉዞ ፤ ያልተጣሉትን ነገዶች ለማግባባትና ሰላም ለማስፈን ሳይሆን፣ የወያኔን ፍላጎት በሕዝቡ ላይ ለመጫን፣ ወያኔ እንደቀደምቶቹ ሁሉ አፈር ቅሞ እንዲነሳ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት መሆኑን ማወቅና ሕዝቡ ከትግሉ እንዳይዘናጋ ማድረግ ብልኅነት ነው።

የለማን የባሕርዳር ጉዞ ከሌላ አቅጣጫም ማየት ተገቢ ነው። እንደሚታወቀው የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅቶች ከ14 በላይ ደርሰዋል። እነዚህ ድርጅቶች በአፈጻጸም ቅደም ተከተልና በትግል ስልት ይለያዩ እንጂ፣ ኦሮሚያ በሚለው የክልል ስም፣ የኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም እንደ ቁመቱን ወርዱ ማግኘት አለበት፣ ኦሮሚኛ የአገሪቱ የሥራ ቋንቋ መሆን አለበት' በልዩነት ላይ የተመሠረተው የቋንቋ ፌዴሬሽን ይቀጥል በሚሉት ዙሪያ ልዩነት የላቸውም። በዚህም የተነሳ ሁሉም የኦሮሞ ድርጅቶች ፣የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ፣ኦሮሞው የፈለገውን ለመሆንና ለማድረግ ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ቢፈልግ የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ወሣኝ ቦታዎችን ይዞ፣ቋንቋው የሥራ ቋንቋ ሆኖ፣ አሁን ያለው በልዩነት ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ መኖር እንችላለን። ይህ ካልሆነ ኦሮሚያን ገንጥለ የራሳችን አገር ለመመሥረት እንችላለን ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረሳቸውን የተለያዩ መረጃዎች ያሳይሉ። እነዚህ አማራጭ ጉዳዩችን ሁሉም የኦሮሞ ድርጅቶች ኦሕዴድን ጨምሮ ይስማሙባቸዋል። ይህ ደግሞ የትግሬ-ወያኔን ከፍተኛ ከሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ከቶታል። ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ይረዳኛል ብሎ ያሰው ስሌት፣ የኦሮሞዎቹ ጥያቄ የሥልጣን ጥያቄ ስለሆነ፣አፋዊ የሥልጣን ቦታዎቹን ማለትም ጠቅላይ ሚኒስተርነቱን የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤነቱን ለእህት ድርጅታችን ለኦሕዴድ አባሎች ሰጥተን፣ የመንግሥት ፖሊሲዎች ማስፈጸሚያ ዋሣኝ ተቋሞች የሆኑትን፣ መከላከያውን፣ ፖሊስን፣ አቃቢ ሕጉን፣ ደኅንነቱን፣ የውጭ ጉዳዩን፣ የኢኮኖሚ ተቋሞቹን፣ወዘተ በኢሕአዴግ ውስጥ ባለን የወሳኝነት ቦታ ተጠቅመን በአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የበላይነቱን ይዘን እንቀጥላለን። በዚህም የመጨረሻ ግባችን የሆነውን የትግራይ ትግርኚ መንግሥት ምሥረታ የሚያስችሉንን ቅድመ ሁኔታዎች አመቻችተን፣ ለትግራይ ትግርኚ ምሥረት፣ ኢሕአዴግ ዕውቅና ሰጥቶ በፊርማ ኤርትራን እንደሸኘት ሁሉ፣ እኛንም እንደዚሁ የሚያደርግ አካል በቀሪዋ ኢትዮጵያ ውስጥ መፍጠር አለብን ብለው በማሰብ፣ ለማን ወይም ግርማ ብሩን በማፈራረቅ፣ ከላይ ለተጠቀሱት ቦታዎች ለማስቀመጥ መዘጋጀታቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ አይሆንም የሚባል አይደለምና ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምነው ወገን ጉዳዩን አጽንዖት ሰጥቶ ሊከታተለውና ከወዲሁ መላ ሊመልልለት ይገባል። ከሁሉም በላይ ዐማራው አንድነቱን አጠንክሮ ይህ ዕቅድ እውን የሚሆነው በርሱ መቃብር ላይ ነውና፣ ከመቀበሩ በፊት ጠላቶቹን ለመቅበር እንኳን ኢትዮጵያዊነት እምነቱና ስሜቱ እንደሚታገሉት አውቆ፣ ላለመቀበር ግን፣ለመታገል ራሱን ዝግጁ ማድረግ ይጠብቅበታል። ለመግደል ዓላማ ባይኖረውም ፣ላለመገደል የመቆም ዓላማ ሊኖረው ግድ ይላል። «ጅብ ከሚበላይ ፣ጅብ በልተህ ተቀደስ» የሚለውን የአባቶቹን መርሆ ማክበር ግድ ከሚል ጊዜ ላይ መሆኑን ማገናዘብ ተገቢና ትክክልም ነው።

ከዚሁ ከለማ መገርሣ የባሕርዳር ጉዞ ቀደም ሲልና በተከታዩም በመቀሌ የወያኔና የብአዴን ተወካዮች ለሰላምና ለመረጋጋት በሚል ስም መሰብሰባቸው ይታወቃል። የወያኔ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትም ፣ወያኔ ሥልጣና ከያዘ ጊዜ ጀምሮ ተከታታይና ረጃጅም ጊዜ የወሰዱ ስብሰባዎች ማድረጋቸው ይታወቃል። በተመሳሳይ ሁኔታ የወያኔ ተወካዮች ከብአዴን ተወካዮች ጋር በጎንደር ከተማ የትግሬን እና የጎንደርን ሕዝብ አንድነትና ሰላም ለማስፈን በሚል ስብሰባ መካሄዳቸው ግልጽ ነው ። ይህ ዓይነቱ ስብሰብም በተለያዩ ክልልሎ እንደሚቀጥል አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ባንድ ቃለምልልስ አረጋግጧል። በለማ መገርሳና በተከታዮቹ ስብሰባዎችም ሆነ በኢሕአዴግ ምክር ቤት የአገሪቱ አውራ ችግሮች ተብለው የተገለጡት «ትምክህተኝነት፣ ጠባብነት እና ኪራይ ሰብሳቢነት» የሚሉት ናቸው። በነርሱ አባባል ጠባብ የሚሉት ሲጠብ ኦነግ፣ ሲሰፋ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አቀንቃኞችን ነው። ትምክህተኛ የሚሉት የዐማራውን ነገድ በድፍኑ ወይም በጥቅሉ ነው። ኪራይ ሰብሳቢ የሚሉት የኢሕአዴግ እህትና አጋር ድርጅቶች የሚሏቸውን በአገዛዙ ውስጥ ውሣኔ የመወሰንና የተወሰነን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በየተቋሙና ድርጅቶች ውስጥ ራሱ ወያኔ መልምሎ ያሰማራቸውን ልምድ፣ ዕውቀትና ክህሎት አጠር የሆኑ ሆዳደር ግለሰቦችን ነው።

እነርሱ እንዳሉት የአገሪቱ ችግሮች ጠባብነት፣ ትምክህተኝነትና ኪራይ ሰባሳቢነት ናቸው ብለን ብንቀበል፣ የነዚህ ችግሮች ምንጫቸው ምንድነው? ብለን ካልጠየቅንና ትክክለኛ መልሱን ለማግኘት ካልጣርን፣ ለችግሮቹ መፍትሔ ልናገኝ አንችልም። እነዚህ ዋነኛዎቹ የአገሪቱ ችግሮች ናቸው ያሏቸው፣ የችግሮቹ መከሰቻ ስበቦች እንጂ፣ በራሳቸው ችግሮች አይደሉም። የችግሮቹ መሠረታዊ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው። የመጀመሪያው አገዛዙ የተከተለው የዘረኛነት አመለካከት ነው። ሁለተኛው በዘረኛ አመለካከት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀው

ሕገመንግሥት ነው። ሦስተኛው ሕገ-መንግሥቱን መሠረት አድርጎ የተዋቀረው በልዩነት ላይ የተመሠረተው የፌደራል የመንግሥት አደረጃጀት ነው። አራተኛው ሕገመንግሥቱን ተግባራዊ ለማድረግ ባሉት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርክቶች ከኃላፊነት እስከ ጽዳት ሠራተኛ ድረስ በዕውቀት ፣በችሎታና በልምድ ሳይሆን፣ በዘረና በፖለቲካ አቋም ላይ ተመሥርቶ ቦታዎቹ መያዛቸው ናቸው።

ይህን በተመለከተ ሟቹ መለስ ዜናዊ ባንድ ወቅት ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ «የእኛን ዓላማ እስካራመደ ድረስ፣ ዘበኛም ሚኒስቴር ይሆናል»ሲል መናገሩ ይታወቃል። በተመሳሳይ ሁኔታ ዘረኝነቱን ሲገልጽ፣ «ከተማረ የዐማራ ምሑር ይልቅ፣ የትግራይን ገበሬ እናምናለን» ማለቱ የሚዘነጋ አይደለም። ስለሆነም ወያኔና አጋር ድርጅቶቹ በተለያየ ጊዜ የአገሪቱ ችግሮች ናቸው ብለው በተደጋጋሚ የሚነግሩንና መፍትሔም ማግኘት ያልቻሉባቸው ጉዳዮች ችግሮቹ ራሳቸው ወያኔዎችና የሚያራምዱት የዘር ፖለቲካ ስለሆነ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ከፈለጉ ራሳቸውን በራሳቸው መግደል ይኖርባቸዋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ፍላጎቱም ሆነ ወኔው የላቸውም። ስለሌላቸውም የሚሰጡት መልስ ችግር ፈጣሪ የሆነውን ግንዱን ሳይሆን፣ በችግር ፈጣሪው ተቀጥላ ወይም ግንዱን ጠምጥሞ በበቀለው ሐረግ ላይ ነው።

ጠባብትን የአገር ችግር መሆኑ ከታመነ፣ ጠባቡ መነው? መጠበብ ሲባልስ ምን ማለት ነው ? ብሎ መጠየቅና ተገቢ መልስ ማግኘት ተገቢ ነው። ጠባብነት ስንል፣ ሁሉም ነገር ለአንድ ቡድን ይሰጥ፣ ሁሉም ነገር በያዚ ቡድን ፍላጎት ይመራ፣ ያ ቡድን የማናቸውም ነገር ፈላጭ ቆራጭ ይሁን ወዘተ ማለት ነው። ጠባብነት ትርጉም ይህ ከሆነ ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉም በእጁ ሁሉም በደጁ አድርጎ የአገሪቱን እጣ ፈንታ ወደ ገደል እየመራት ያለው የትግሬ-ወያኔ ነው። ዐማራን በጠላትነት ፈርጆ፣እርሱን በማጥፋት የትግራይ ረፐብሊክ እመሠርታለሁ ብሎ የተነሳ ጠባብ ድርጅት ወያኔ ነው። ወያኔና ተከታዮቹ ሌሎችን ጠባብ ሲሉ ምን ያህል የኢትዮጵያን ሕዝብ የማመዛዘን ችሎት ዝቅ አቀድርገው እንደሚመለከቱት ያሳያል ፤«ብሣና ይነቅዛል ወይ? ቢሉት ለእንጨቱ ሁሉ ማን አስተማረው፣» ብሎ መለሰለት እንደሚባለው፣ በጠባብነት አመለካከት ከተማመን፣ ጠባቡ ወያኔ፣ የመጥበብ አስተማሪውም የትግሬ-ወያኔ ነው። እናም ጠባብነትን ለመዋጋት ጠባቡ የትግሬ ወያኔ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ማዕከል መወገድ አለበበት። ይህ ዕውን እንዲሆንም የጠብባ አመለካከት ምንጭ የሆነው ሕገ መንግሥትና በርሱ ላይ የተመሠረተው የፌደራል የመንግሥት አደረጃጀት በሌላ መተካት አለበት።

ትምክህተኝነት በወያኔዎቹና በተከታዮቹ አንዱ የአገሪቱ ችግር እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። በነለማ መገርሳና ገዱ አንዳርጋቸው፣ በረከት ስምዖን በስፋት ተነግሯል። ከላይ ለማለት እንደተሞከረውም፣ በትምክህተኝነት መኖር እንስማማና፣ ትምክህተኝነት ምን ማለት እንደሆነ፣ ይህንስ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ማን እያደረገ እንደሆነ በተጨባጭ እንፈትሽ። ትምክህተኝነት አንድና ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮች፣ ሌሎች የሌሏቸው ያ ትምክህተኛ የሚባለው አለኝ ወይም አሉኝ የሚላቸው ነገሮች መኖር ነው። በመሆኑም ትምክህተኝነት ባለ ፣ በጨበጡት ነገር የእኔ ነው ብሎ መመካት ነው። ከዚህ አንፃር ኦሮሞዎቹ በቁጥራቸው፣ ወያኔ የናንተነው ብሎ በሰጣቸው የቆዳ ሥፋት፣ በገዳ አደረጃጀታቸውና በባህላቸው፣ ወዘተ ሊመኩ ይችላሉ። ዐማራው በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በኢትዮጵያዊነት እምነቱ፣ በቁጥሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በጽሑፍ ቋንቋው፣ እስከሁን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ነገድን መነሻና መድርሻ አድርጎ ለመደራጀት ባለመፍቀዱ፣ ባለፉት አገዛዞች እንደሕዝብ የተለያዩ ችግሮች ተሸካሚ ሆኖ እያለ፣ ሌሎች በጠላትነት ፈርጀው ሊያጠቁት ሲነሱ፣ እርሱ በሆደ ሠፊነት መያዙ ወዘተ ትምክህተኛ ሊያሰኙት ይችላሉ። በእርግጥም ሁለቱ ነገዶች ከላይ በተጠቀሱት ይመካሉ። ባለው፣ በያዙት መመካት ከአናት በላይ ሲንርና ሌሎችን ድንክየ አድርጎ ወደ መመልከት ሲያዘነብል በትክክል ትምክህተኝነት የአብሮነት ጠር ነውና ሊወገዝ ይገባዋል። እራስን መሆንና በራስ መተማመን ግን ሊደገፍና ሊበረታታ የሚገባ እንጂ፣ ሊወገዝ የሚገባው አይሆንም። ለአብሮነት ጠር አይደለምና።

ከነዚህ ተነስተን የወያኔን ማንነት እንፈትሽ። ወያኔ ከመነሻው ጠባብና ማን አህሎኝነት የተጠናወተው የአንድ ዘር ድርጅት ነው። ፕሮግራሙ ዐማራን ማጥፋት አለብኝ ብሎ የተነሳ ነው። በዚህ ሀሳቡ፣ እቅዱና ተግባሩ ተጣጥመው 5 ሚሊዮን ዐማራ ከምድረገጽ አጥፍቷል። ኢትዮጵያን አፍርሽ በራሴ አምሳል እገነባታለሁ ብሎ አቅዶ፣ ይኸውና ዛሬ ለዘመናት በአንድነት ተባብረው የኖሩ የዐማራና የኦሮሞ፣ የኦሮሞና የሶማሊያ፣ የትግሬና የዐማራ ወዘተ ነገዶን ደም እያቃባና የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እየፈጸመ መሆኑ ይታወቃል። ከሁሉም በላይ ኤርትራና አስገንጥሎ፣ አገሪቱን ካለወደብ አስቀርቶና የሌሎች አገሮች ጥገና አድርጎ፣ ሕዝቡን በዘር ከፋፍሎ ጥሩ ሠራሁ እያለ የሚመካ ነው። በአገር አፍራሹ ሕገመንግሥት ከመጠን በላይ የሚመካ,ነው። አገር ለማፍረስ በሠራው ሥራ ተመክቶ፣ ያን አገር አፍራሽ ትውልድ «ተራራውን ያንቀጠቀጠ» ሲል መጽሐፍ የፃፈ ነው። የትግሬ ወያኔ ከኢትዮጵያ ሥልጣን ከተወገደ አገር ይፈርሳል፣ የሁሉም ነገር ፈጣሪዎች እኛ ትግሬዎች ነን በማለት የሚመካ ነው። ከዚህ አንፃር በዛሬዩቱ ኢትዮጵያ ትምክህተኛው የትግሬ ወያኔ ቡድን ነው። ይህ ቡድን በእርግጥም ትምክህተኛ ነው። ትምክህቱ ደግሞ ለሰላምና አብሮ ለመኖር ካንሰር ነው። ይህ ካንሰር ግን የበሽታው መነሻ አይደለም። በሽታውን አክሞ ለማዳን የበሽታው ሕዋስ መፈልፈያ መታወቅ አበት። የዚህ በሽታ መፈልፈያ ምቹ ሁኔታ ወያኔ የሚያቀነቅነው የዘር ርዕዮተ-ዓለም እና በዚህ ርዕዮት የተዘጋጀው ሕገመንግሥትና ሕገመንግሥቱን በሥራ ላይ ለማዋል የተደራጀው የልዩነት የፌደራል አደረጃጀት ነው።

ሌላው በወያኔ ጀሌዎች እንደበቀቀን በየቀኑ የሚለፈፈው ያገሪቱ ችግር በእነርሱ አጠራር «ኪራይ ሰብሳቢነት» ሲሉ ስም ያወጡለት አስነዋሪ የዘረፋ ተግባር ነው። ኪራይ ሰብሳቢነት ማለት፣ ሙስና ፣ጉቦ፣ ሕጋዊ አሠራሩንና መንገዱን ትቶ በገንዘብና በጥቅም ሕጋዊ ያልሆነውን መከተልና ማስፈጸም ማለት ነው። ሙስና ወይም ጉቦ የሚከተለው የታወቀ ጠገግ አለው። የጠገጉ ምሽግ ደግሞ ሥልጣን ነው። ይነስም ይደግ የመወሰንና የማድረግ ሚና የሌለው ሰው ጉቦ ሊቀበል ወይል ሊበላ አይችልም። ሙሰኛ ወይም ጉቦኛ ወይም በነመለስ አባባል ኪራይ ሰብሳቢ ለመሆን ካንድ መዋቅር ቦታ መቀመጥን የግድ ይላል። በአገሪቱ ላሉት መንግሥታዊ መዋቅሮች ደግሞ ምደባ ወይም ሹመት የሚሰጠው የወያኔ የሚኒስትሮች ካቢኔ ጀምሮ በየደረጃው የተዋቀሩት የፌደራልና የክልል መንግሥታት ተብየዎች ናቸው። ተመዳቢዎቹ

,ወይም ተሿሚዎቹ ደግሞ የሚመረጡት በዕውቀት፣ በዜግነት፣ በችሎታ በውድድር  ሳይሆን፣ በኢሕዴግ እህት ድርጅቶች በተለይም በወያኔ ድርጅት አባልነትና ይሁንታ ተበጥረው ነው። እንግዲህ ኪራይም በሉት ጉቦ የሚሰበስቡት እነዚህ በዘር ፣ በዝምድና፣ በጋብቻ፣ የተሳሰሩ ሰዎች ናቸው። ችግሩ የኪራይ ሰብሳቢነት መሆኑ ከታመነበት ምንጩ የኢሕአዴግ ፖሊሲ ነው። የፖሊሲው ምንጭም ሕገመንግሥቱ እና የመንግሥት አደረጃጀቱ ነው። ስለሆነም ችግር ናቸው ተብለው ለታመነባቸው ጉዳዮች መፍትሔው ወያኔና ሥርዓቱን ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ማዕቀፍ ውስጥ ማስወጣት ነው።

ዕውነታው ይኸ ሆኖ እያለ ከአብርሃና ኢዛና፣ ከካሌብ እስከ ዐፄ አምደጽዮን፣ ከዐፄ ናዖድ እስከ ዘመነ ደርግ ድርሰ ውኃና ወተት ሆነው የኖሩትን ኢትዮጵያውያን ነገዶች አንድ እናድርጋችሁ፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ይመሥረት እያሉ በየቦታ መደገሥ ሁለት ተግባሮችን ከማስፈጸም ባሻገር ሌላ ጥቅም ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብ። የመጀመሪያው የትግሬወያኔ የፈለገውን እንዲያደርግ ጊዜ መግዣ አንጻራዊ መረጋጋት መፍጠርና የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ማስለወጫ ነው። ሁለተኛው በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ስም ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ለመዝረፍና በመዋቅር ለተደራጁት ኪራይ ሰብሳቢዎች ሠፊ የብዝበራ በር መክፈት ነው። ምክንያቱን የአገሪቱ ችግሮች ወያኔና ሥርዓቱ እንጂ፣ የነገዶች ጠብ አይደለም። ስለሆነም የተቀጣጠለው ሕዝባዊ እንቢተኝነት ጥያቄ፣የችግሮቹን ስበቦች ወይም ተቀጥላዎች ሳይሆን፣ ምንጩ የሆነውን የትግሬ ወያኔን አገዛዝ ይወገድ ነው። ለዚህም 2010 የወያኔ መወገጃ እንጂ፣ እንዳለፉት ሁሉ በቃላት ሽንገላና በችግሮቹ ቅርጫፎች ላይ በሚሰጡ ማባበያ መልሶች  በመዘናጋት እንደ እባብ አፈር ልሶ መነሻው እንዳያደርገው ነቅተን በመጠባበቅ የዘመመውን የወያኔ አገዛዝ ተጠናክሮ በመግፋት ወደ ግባተ መሬቱ መክተት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥረት ሊሆን ይገባል።!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ኅብረት ተጠብቃ ለትውልድ ተሸጋገራለች!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!